የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፬

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.45
ADDIS ABABA 14th July, 2022

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፪/፪ሺ፲፬

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለምአቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.........................................................................ገጽ ፲፬ሺ፫፻፺፯

## Content

Proclamation No.1272/2022

International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for financing Rural Financial Intermediation Programme III (RUFIP III) Project Ratification Proclamation …..........................................................................Page 14397

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፪/፪ሺ፲፬

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፫ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በጣሊያን ሮም ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም በአካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1272/2022

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to three million six hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 3,600,000.00) for financing Rural Financial Intermediation Programme III (RUFIP III) Project, was signed in Rome, Italy on 8th Day of January, 2020;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on 17th Day of May, 2022;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፪/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በጣሊያን ሮም ከተማ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2000003211 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.<u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር (፫ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1.<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for financing Rural Financial Intermediation Programme III (RUFIP III) Project Ratification Proclamation No. 1272/2022".

**2.<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 2000003211 signed in Rome, Italy on 8th Day of January, 2020, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified.

**3.<u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to three million six hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 3,600,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4.<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this Day of July 14th, 2022.**

**SAHALE - WORK ZEWEDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**